Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 7 ፤ ጥር 2011 ዓ.ም.

በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞቹ የሚሰራጭ

## ለ60 ዓመታት ከሐምሊኖች ጋር የዘለቀ የዓላማና የመንፈስ ፅናት



"...ጥቂት ቁጭ ብዬ አብሬያት ካለቀስኩ በኋላ እማዬ አይዞሽ በህይወት እስካለሁ በነፃም ቢሆን አገለግልሻለሁ ዓላማሽም ይሳካል አልኳት። ተነስታ አቀፈችኝና አመሰገነችኝ..."

## በውስጥ ገፆች


- መልዕክት 2
- የስኬት ጉዞ 3
- የሀዘን መግለጫ 4
- የብድር አገልግሎት 5
- የቢቂላ ሽልማት 6
- ጋሼብሩ 7
- ታላቁ ሩጫ 10
- የወደፊት አቅጣጫ 11

# መልዕክት

## ከ ተ/ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ



ውድ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች! እንኳን ለድርጅታችን 60ኛ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ፤አደረሰን እላለሁ! የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ መስራች የሆኑት ዶ/ር ካትሪን ሐምሊንና ባለቤታቸው ዶ/ር ሬጅ ሐምሊን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሁሉን አቀፍ የፊስቱላ ህክምና አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ እነሆ 60 ዓመት ሞላ፡፡

ይህን 60ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ለዶ/ር ካትሪንና ሐምሊንና የእሳቸውን ራዕይ ለማሳካት ከጎናቸው ለቆማችሁ ለድርጅታችን ሠራተኞች ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡ በሞት ለተለዩን ባለቤታቸው ዶ/ር ሬጅ ሁሌም ነብሳቸው በገነት ትኑር ዘንድም ምኞቴ ነው፡፡

ባለፉት 60 ዓመታት ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በአገራችን ብሎም በዓለማችን የእናቶች ጤና ክብካቤ ስርዓት ትልቅ አሻራ የጣለ ድርጅት ነው፡፡ ከ60 ሺህ በላይ እህቶቻችንና እናቶቻችን በድርጅታችን እርዳታ አማካኝነት ከፊስቱላ ጉዳት ተፈውሰው ከማህበረሰባቸው ጋር ተቀላቅለዋል፡፡ ለዚህም መሳካት ደግሞ በዋናው ሆስፒታል፣ በአምስቱ የክልል ማዕከላት፣ በኮሌጅና በደስታ መንደር ያገለገሉና እያገለገሉ ያሉ ሠራተኞቻችን ድርሻ የጎላ በመሆኑ ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የዶ/ር ካትሪን ሐምሊንና የባለቤታቸውን የዶ/ር ሬጅ ሐምሊንን ራዕይ ሙሉ በሙሉ ለማሳካትና የእነሱንም ሌጋሲ ለማስቀጠል አዲስ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ዕቅድ መሳካት የመላው ሠራተኛ የተለመደው ጥንካሬ፣ትጋትና ርብርብ ወሳኝ ነው፡፡

በድጋሚ እንኳን ለድርጅታችን 60ኛ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ የዶ/ር ካትሪን ሐምሊንና የባለቤታቸውን የዶ/ር ሬጅ ሐምሊን ራዕይ ሙሉ በሙሉ ለማሳካትና የእነሱንም ሌጋሲ ለማስቀጠል ሁሉም ሠራተኛ መለያችን የሆነውን አብሮነት አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

## የ60 ዓመታት የስኬት ጉዞ
## እ.አ.አ ከ1959-2019




ዶ/ር ካትሪንና ዶ/ር ሬጅ ሐምሊን በአውስትራሊያ ሲድኒ ውስጥ ከሚገኙ ስመ ጥር ሆስፒታሎች በአንዱ ውስጥ በአዋላጅነትና በማሕጸን ስፔሻሊስትነት የሚያገለግሉ ሃኪሞች ነበሩ::

እ.አ.አ በ1957 “ዘ ላንሰት” በተባለው የእንግሊዝ የጤና መጽሔት ላይ የወጣው ማስታወቂያ፡- “አዲስ አበባ የሚገኘው የልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ነርሶችን በአዋላጅነት የሚያሰለጥን ት/ቤት ለማቋቋም የማሕጸን ዶክተሮችን ለመቅጠር ይፈልጋል” ይላል::

የሃኪሞች እጥረት ባለባቸው ሃገሮች ውስጥ የመስራት ፍላጎት የነበራቸው ሐምሊኖች ማስታወቂያውን እንዳነበቡ ለቦታው አመለከቱ:: በወቅቱ የነበረው የቀ.ኃ.ሥ መንግስትም ማመልከቻቸውን ተቀበለ::የስድስት ዓመት ሕጻን ልጃቸውን ሪቻርድ ሐምሊንን ይዘውም እ.ኤ.አ. በ1959 አዲስ አበባ ገቡ::

እንሆ ሐምሊኖች ለ60 ዓመታት የዘለቀውን የህይወት አድን ተልዕኮ የጀመሩት በዚህ መልክ ነበር:: ለሦስት ዓመት የፈረሙት የኮንትራት ሥራ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ በማስቆጠር ላይ በሚገኘው የሕይወት ማዳን ተልዕኮ ተቀይሮ ይገኛል:: የዓላማና የመንፈስ ጽናት ያላቸው ሐምሊኖች ከምንም ተነስተው በከፈሉት ወደር የሌለው መስዋእትነት ዛሬ ከ60,000 ሺህ

በላይ ሴቶች ወገኖቻችን ከዚህ ~ አግላይ ህመም ተፈውሰው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለዋል።

በዚህ አጋጣሚ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የቦርድና የማናጅመንት አካላት የዶ/ር ካትሪንና ዶ/ር ሬጅ ሐምሊን ህልም ለማሳካት ከጎናቸው ለቆሙ ለመላው ለድርጅቱ ሰራተኞች ምስጋናቸውን ያቀርባሉ።

## የሃዘን መግለጫ





እኛ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች በእህታችን ወ/ሮ ሉባባ መሀመድ ህልፈተ ህይወት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን መግለጽ እንፈልጋለን።

በ1975 ዓ.ም የተወለዱት ወ/ሮ ሉባባ መሀመድ ባደረባቸው ህመም በህክምና ሲረዱ ቆይተው ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል። ወ/ሮ ሉባባ በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የፊስቱላ ህክምና ካገኙ በኋላ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በደስታ መንደር በኮንትራት በኋላም በቋሚነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

በዚህ መሪር የሀዘን ወቅት ለቤተሰቦቿና ለወዳጅ ዘመዶቿ በሙሉ መጽናናቱን እየተመኘን እግዚአብሔር ነብሷን በገነት ያኑሪልን ዘንድ እንጸልያለን።

# ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ለሠራተኞቹ የባንክ የብድር አገልግሎት አመቻቸ

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ለሠራተኞቹ ከወጋገን ባንክ ለቤት መግዣና ጅምር ቤት ማስጨረሻ፣ ለመኪና መግዣና ለፍጆታ ዕቃ የሚውል የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ውል ተፈራረመ፡፡ የብድሩ መመቻቸት መሰረታዊ የሠራተኞችን ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር፣ የሠራተኞችን የስራ ተነሳሽነትና ከሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ትስስር ያሳድጋል ተብሎ ይገመታል፡፡





በተገባው ውል መሰረትም ሠራተኞች የብድር አገልገሎት ለማግኘት እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የገለጹት የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የሰው ሃይል ልማትና አስተዳደር ኃላፊ አቶ ተስፋዬ አባይነህ፣ ሰራተኞች ብድሩን ለማግኘት መከተል ያለባቸውንም ሂደትም አመላክተዋል፡፡

**ሂደት 1፡**

ከሰው ሃይል ልማትና አስተዳደር ክፍል ደብዳቤ ወደ ባንክ ማጻፍ

**ሂደት 2፡**

ከባንክ ወደ ሚፈልጉት ክፍለ ከተማ ገቢዎችና ጉሙሩክ ቢሮ ደብዳቤ በማጻፍ የታክስ ክሊራንስ መውሰድ

**ሂደት 3፡**

አስፈላጊውን ዶክመንቶች / የደመወዝ መጠን የሚገልጽ ደብዳቤ፣የግዥ ውል ስምምነት፣የታክስ መለያ ቁጥርና ክሊራንስ፣ የጋብቻ ሰርቴፍኬት… / ለባንክ በማስገባትና ቀጣይ የባንኩን ሂደት በመከተል ብድሩን ማግኘት

**በመጨረሻም፡**

የቤት እና/ወይም የመኪና ባለቤት መሆን

## ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን የቢቂላ ሽልማት አሸናፊ ሆኑ

መስከረም 12፣ 2011 ዓ.ም ካናዳ ቶሮንቶ ላይ የተካሄደው 5ተኛው ዙር የቢቂላ ሽልማት ስነስርዓት ዶ/ር ካትሪንንና ባለቤታቸው በኢትዮጵያ በመሰረቷቸው የፌስቱላ ህክምና ተቋም በወሊድ ምክንያት የፊስቱላ ተጎጅ ለሆኑ ኢትዮጵያውያን ለረጅም ዓመታት እየሰጡ ላሉት ነፃ የህክምና አገልግሎት እውቅና በመስጠት በህክምናና በበጎ አድራጎት ዘርፍ የዓመቱ ተሸላሚ አድርጓቸዋል፡፡




ዶ/ር ካትሪንን ወክለው በስነስርዓቱ የተካፈሉት የድርጅታችን ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ማሞ ሽልማቱን በተረከቡበት ወቅት ተሳታፊዎችን አመስግነው ሽልማቱ ለዶ/ር ካትሪን የህይወት ዘመን አስተዋፅኦ እውቅና የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር አሁን በድርጅቱ እየሰሩ ለሚገኙት ሰራተኞች ተጨማሪ ጉልበት ይሆናቸዋል ብለዋል፡፡ ተጠባባቂ ዋና ስራ አስፈፃሚው አክለውም ይህን የመሰለ ደማቅ ስነስርዓት ያዘጋጁትን አካላት በዶ/ር ካትሪን ስም አመስግነዋል፡፡

የቢቂላ ሽልማት በካናዳ በሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አማካኝነት የተቋቋመ የሽልማት ድርጅት ሲሆን ዓላማውም በትምህርታቸው፣ በሙያቸው፣ በንግድ ስራ ፈጠራቸው እና በበጎ አድራጎት ተግባራቸው የጎላ ስራ ያሳዩ እና ለኢትዮጵያውያን የሚተርፍ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ግለሰቦችን በመሸለም ወጣቱን ትውልድ ማነቃቃት እና ስኬታማ ማድረግ ነው፡፡

# የ60 ዓመት የስኬት ጉዞ ጅማሬ



ልክ እንደመስራቾቹ ሁሉ እሳቸውም የሐምሊንን ቤተሰብ የህይወት አድን ጥሪ ከተቀላቀሉ 60 ዓመት ሞላቸው። ከሐምሊን ቤተሰብ ጋር ከልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ጀምሮ የአዲስ አበባ ዋናው ሆስፒታል ምስረታን ተሻግሮ አሁንም ድረስ የዘለቀ ቤተሰባዊ ትስስር ፈጥረዋል። ለእሳቸው ሐምሊን የስራ ቦታቸው ብቻ አይደለም። በመስራቾቹ በጎ ዓላማ ተማርከው ወጣትነታቸውን የገበሩለት፣ ቤተሰብ መስርተው ልጆች አፍርተው የከበሩበት፣ በጥቅሉ አብዛኛው የህይወታቸውን ምዕራፍ ያሳለፉበት ቤታቸውም ጭምር እንጂ። ከሐምሊን ቤተሰብ የ60 ዓመት የስኬት ጉዞ ጋር ስማቸው ጎልቶ ከሚነሱት ግለሰቦች መካከል ከቀዳሚዎቹ አንዱ ናቸው።

ውድ አንባቢዎቻችን፣ መቼም ስለማን ማንሳት እንደፈለግን ሳትገምቱ አልቀራችሁም። አዎ በዚህ የ60 ዓመት የስኬት ጉዞአችንን ለማክበር እየተዘጋጀን ባለንበት ወቅት የዚህ ሁሉ ስኬት መነሻ ምን ይመስል እንደነበር እንዲያጫውቱን ጠይቀናቸው በደስታ ቀጣዩን ቃለመጠይቅ የሰጡን የ80 ዓመቱ እድሜ ባለፀጋ ጋሼ ብሩ ናቸው። ፈቅደው ስላጫወቱን ጋሼ ብሩን እናመሰግናለን።

**ጥያቄ:** ከሐምሊን ቤተሰብ ጋር እንዴት ሊተዋወቁ ቻሉ?

**ጋሼ ብሩ:** በወቅቱ ስራ ፈላጊ ስለነበርኩ ልዕልተ ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ይሰሩ ከነበሩት ሐምሊኖች ጋር ለምትሰራ ዘመዴ ስራ እንድትፈልግልኝ ስጠይቃት እራሴ መጥቼ አባዬን(ዶ/ር ሬጅ) እንድጠይቃቸው አደፋፈረችኝ። መጀመሪያ ለእኔ የሚሆን ስራ እንደሌላቸውና ሲኖር እንደሚጠሩኝ ነግረውኝ ሸኙኝ። በኋላ ቃላቸውን ጠብቀው በወንድሜ በኩል ጠሩኝ።

**ጥያቄ:** የልዕልት ፀሐይ ቆይታዎ ምን ይመስል ነበር?

**ጋሼ ብሩ:** የጥንዶቹ የስራ ፍላጎት የሚገርም ነበር። ለታካሚዎቹ የሚሰጡት ፍቅር ይለያል። ከሀገራቸው ጭምር መድሀኒቶችን

እያስመጡ ያክሙ ነበር፡፡ አንድ ወቅት ትዝ የሚለኝ አባዬ ለመድሀኒት ማስቀመጫና ለቢሮ የሚያገለግሉ ክፍሎች ማሰራት ፈልገው ገንዘብ ስላልነበራቸው እኔን ጠርተው ጎጆዎችን እንድሰራ አዘዙኝ፡፡ ሰርቼ እኮ አላውቅም ብላቸውም ከተሞከረ የማይቻል ነገር የለም ብለው አደፋፈሩኝ፡፡ በመጨረሻም ለራሴ አስኪገርመኝ ድረስ ጥራት ያላቸው በክረምት እንኳን የማያንጠባጥቡ አምስት የሳር ክዳን ቤቶችን ሰራሁ፡፡ ልጃቸው ሪቻርድ ያኔ ህፃን ነበር፡፡ ቤቶቹን 'የብሩ ሰፈር' ይላቸው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ የነሱ የስራ ባህል ተጋብቶብኝ የማልሰራው ስራ አልነበረም ፤ አትክልተኛ ፤ፋርማሲስት፤ግዢ፤ጉዳይ ፈፃሚ ብቻ ምን አለፋህ ሁለገብ ነበርኩ፡፡ ይሄን ሁሉ ስሰራ ታዲያ የምንግባባው በምልክት ነበር፤ ቋንቋቸውን አልችልማ፡፡



**ጥያቄ፡** የአዲስ አበባው ፊስቱላ ሆስፒታል ሲመሰረት የነበረውን ሁኔታ እስቲ ያጫውቱኝ

**ጋሼ ብሩ፡** ሐምሊኖች ሁል ግዜም የሚያልሙት የፊስቱላ ታካሚዎች ሳይሸማቀቁ በነፃነት የሚታከሙበትን ሁኔታ መፍጠር ነበር፡፡ ትዝ ይለኛል ሲቲ የምትባል የፊስቱላ ተጎጂ አክመው ካዳኑ በኋላ ፎቶ አንስተው ወደ ሀገራቸው በመሄድ ብዙ ገንዘብ አሰባስበው በመመለስ አሁን ሆስፒታሉ ያለበትን ቦታ ገዝተው ግንባታ አስጀመሩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለየብቻ ሌላ ጊዜ ደግሞ አብረው ባህር ማዶ እየተመላለሱ በመለመን ግንባታውን ወደማጠናቀቅ ተቃረቡ፡፡ በዚህ መሀል የመንግስት ለውጥ

በመካሄዱ ወዳጅ የነበሩት አፄ ኃይለ ሥላሴ ከስልጣን ወረዱ፡፡ ልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታልም ፈረሰና ያለበቂ ቅድመ ዝግጅት በግንባታ ላይ ያለው ሆስፒታል ሙሉ ለሙሉ ሳይጠናቀቅ የፊስቱላ ታካሚዎች እንዲገቡ ተደረገ፡፡ ቀደም ሲል በልዕልት ፀሐይ መንግስት ያቀርብ የነበረው በመቋረጡ በወቅቱ ከባድ ፈተና የነበረው ታካሚዎቹን መመገብ ነበር፡፡ በኋላ እኔን ጠርተው ምን እናድርግ ሲሉኝ ከባልንጀራዬ ጋር በመመካከር ከምግብ ቤት አንድ ምግብ በ 15 ሳንቲም በዱቤ ለማቅረብ ተስማምተን የሆስፒታሉ ወጥ ቤት እስኪጠናቀቅ ድረስ ጠዋትና ማታ ምግብ በሸክም ኮካ አካባቢ ከሚገኘው ምግብ ቤት እየተመላለሰ ለታካሚዎች ሲቀርብ ቆየ፡፡ በኋላ ወጥ ቤቱም ተቋቋመ፤ አስፈላጊው ሁሉ ተሟላና የምግብ ቤቱ ውል ተቋርጦ እዚሁ የተዘጋጀ ምግብ መቅረብ ጀመረ፡፡

**ጥያቄ:** በ60 ዓመት ቆይታዎ የማይረሱት አጋጣሚ ምንድን ነው?

**ጋሼ ብሩ:** አሳዛኝ ቢሆንም ሁሌ ከአእምሮዬ የማይጠፋው አባዬ ካረፉ በኋላ አንድ ቀን ጠዋት ወደ እማዬ ቤት ስወርድ እማዬ በር ላይ ቁጭ ብላለች፤ተስፋ መቁረጥ ይታይባታል፤እንባዋ ያለማቋረጥ ዝም ብሎ ይፈሳል፡፡ ጥቂት ቁጭ ብዬ አብሬያት ካለቀስኩ በኋላ እማዬ አይዞሽ በህይወት እስካለሁ በነፃም ቢሆን አገለግልሻለሁ አላማሽም ይሳካል አልኳት፡፡ ተነስታ አቀፈችኝና አመሰገነችኝ፡፡ ከጊዜ በኋላ ግን የሚገርም ጥንካሬና ብርታት በማሳየት ስራው አሁን የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ አደረገች፡፡ እኔም ከጡረታ በኋላም ጭምር ስራዬን እንድቀጥል አድርጋ አሁንም እያገለገልኩ እገኛለሁ፡፡



# የታላቁ ሩጫ ተሳትፎ



የሐምሊን የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዓመታትን ያስቆጠረ ተሳትፎ ዘንድሮም ቀጥሏል፡፡ ባሳለፍነው ህዳር 9፣ 2011 ዓ.ም በተከናወነው የታላቁ ሩጫ ሐምሊን ከአውስትራሊያ የገንዘብ ድጋፍ አሰባስበው በመጡ 14 የካትሪን ሐምሊን ፊስቱላ ፋውንዴሽን ዓመታዊ ጉዞ ተሳታፊዎችና በሚድዋይፈሪ ኮሌጃችን ተማሪዎች ተወክሏል፡፡

በመሮጫ ቲሸርት ማለቅ ምክንያት እንደቀደሙት ዓመታት ከአጠቃላይ ሠራተኞች በሩጫው የተወከሉ ተሳታፊዎች ባይኖሩም ሐምሊን ግን በሌሎች ተወካዮቹ መሳተፉ ሁሉንም ያስደሰተ ሆኗል፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ ሯጮች የተሳተፉበት የዘንድሮው ታላቁ ሩጫ በቅርቡ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረውን እርቀ-ሰላም ተከትሎ በርካታ ኤርትራዊያንና ታዋቂ አትሌቶችን ያካተተ መሆኑ ልዩ አድርጎታል፡፡

# የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

## በቀጣይ ዓመታት ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በሦስቱ ዋና ፕሮግራሞቹ ሊያከናውናቸው ካቀዳቸው መካከል

### ህክምና ፕሮግራም

የሴቶች ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል መገንባት

### መከላከል ፕሮግራም

(ሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ) የማስተርስ ፕሮግራም በክሊኒካል ሚድዋይፈሪ መጀመር

### ማገገምና መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም

የሴቶች አቅም ማጎልበቻ ማዕከል መገንባት

60 years | Hamlin Fistula Ethiopia

የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡

*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*

Hamlin Fistula Ethiopia

*Designed & Printed by Everest Printers*